# የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት

# ደቡብ ኢትዮጵያ ነጋሪት ጋዜጣ

# DEBUB ETHIOPIA NEGARIT GAZETA

# OF THE SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE

፪ኛ ዓመት ቁጥር13
አርባ ምንጭ ታህሳስ 5ቀን ፪ሺ፲፮ዓ.ም

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No 13
Arba minch December. 2023


## አዋጅ ቁጥር ፳፩/፪ሺ፲፮ ዓ.ም

## የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ

### መግቢያ

ቁጠባንና ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ፣ታክስ ከመክፈል ለመሸሽ ወይም በህጉ ውስጥ የሚታየውን ክፍተት በመጠቀም ታክስን ላለመክፈል የሚደረገው ጥረት ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ፣የኢኮኖሚ እድገትን ለማፋጠን እና በጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርትና በመንግስት ገቢ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሻሻል የተጨማሪ እሴት ታክስ ስራ ላይ እንዲውል ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በንግድ ግንኙነት ውስጥ ፍትሀዊነትን ለማስፈን፣ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገቡ ሰዎች ግዴታቸውን እንዲወጡ እና የታክስ ስርዓቱን ሽፋን የተሟላ ለማድረግ የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## PROCLAMATION NO 21/2023

## TURNOVER TAX PROCLAMATION THE SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE

### *Preamble*

*Where as,* it has been determined that there shall be enacted a value-added tax to enhance saving and investment, minimize the damage that may be caused by attempts to avoid or evade taxes, stimulate economic growth, and improve the relations ip between Gross Domestic Product and Government Revenue;

*Whereas,* it is necessary to enact a Turnover Tax Proclamation to ensure fairness in business relations, to enable those not registered for Value Added Tax to fulfill their obligations, and to ensure complete coverage of the tax system;

ከፌደራል የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ጋር የተጣጣመ፣ከሀገሪቱ የታክስ ስርዓት ጋር የተዋሀደ እና ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚሄድ አዋጅ ማውጣት በማስፈለጉ፣

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት በክልል ሕገ መንግስት አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ **"የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 21/2016"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. ትርጉም**

በዚህ አዋጅ ውስጥ ትርጉም ያልተሰጠባቸው ቃላትና ሀረጎች በፌዴራል የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 1341/2016 ውስጥ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1) **"የክልል መንግስት"** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ነው፤
2) **"ቢሮ"** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ገቢዎች ቢሮ እና እንደአግባብነቱ በየአስተዳደር እርከኑ የሚገኙ መምሪያዎች፤ ጽ/ቤቶች እና የታክስ ማዕከላትን ይጨምራል፤
3) **"የገቢ ግብር አዋጅ"** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 19/2016 ነው፤

*Whereas,* it is necessary to issue a proclamation that is consistent with the federal Turnover Tax Proclamation, integrated with the country's tax system, and in line with the actual situation of the region.

**Now, Therefore,** the South Ethiopia Regional State Council has issued this proclamation in accordance with Article 54 sub Article 3/a/ of the constitution of the Region.

## SECTION ONE
## GENERAL

1) **Short Title**

This Proclamation may be cited as the **"Turnover Tax Proclamation No.21/2023"**

2) **Definitions**

For the purpose of this Proclamation, unless defined otherwise in this Proclamation, terms used herein shall have the meaning as defined in the Value-Added Tax Proclamation No. 1341/2024. In addition, unless the context requires otherwise, in this proclamation:

1) **"Regional State"** means South Ethiopian Regional State;
2) **"Bureau"** means the Revenue Bureau of the South Ethiopia Region as well as the departments and office at each administrative level;
3) **"Income tax proclamation"** means South

4) **“ታክስ”** ማለት ዕቃዎች ወይም የአገልግሎቶች ሽያጭ በተከናወነ ቁጥር የሚከፈል ተርን ኦቨር ታክስ ነው፤

5) **“ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ”** ማለት የወጪ ተቀናሽ ሳይደረግ የተገኘ ጠቅላላ ገቢ ሲሆን የተሸጡት ዕቃዎች የተመረቱበትን ወይም የተገዙበትን ዋጋ ይጨምራል፤

6) **“ታክስ የሚከፈልበት ግብይት”** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀፅ 7 ከተርን ኦቨር ታክስ ነፃ ከተደረገው ግብይት በስተቀር በንግድ ስራ ሂደት ወይም የንግድ ስራን እንቅስቃሴ ለማሻሻል በሚደረግ ጥረት ዕቃዎችን ማቅረብ ወይም አገልግሎቶችን መስጠት ነው፤

7) **“ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገበ ሰው”** ማለት በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 1341/2016 አንቀጽ 12 መሰረት ወይም የፋይናንስ ቢሮ ከሚወስነው መጠን በታች በመሆኑ ከተቀመጠው ገደብ ጋር ያልተገናኘ ሰው ወይም በአንቀጽ 13 በፈቃደኝነት ለመመዝገብ ማመልከቻ ባለማቅረብ ምክንያት ወይም በፈቃደኝነት ያልተመዘገበ ሰው ነው፤

8) **“ድርጅት”** ማለት የንግድ ስራን የሚያካሂድ ማንኛውም ኩባንያ፣ የተመዘገበ የሽርክና ማህበር ወይም ከተመዘገበ የሽርክና ማህበር ጋር ተመሳሳይ የሆነና በውጭ አገር ህግ መሰረት የተቋቋመ ድርጅት ወይም ማናቸውም የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የገንዘብ ድርጅት ሲሆን በውጭ ሀገር ያለን አካል በመወከል በክልሉ ውስጥ የንግድ ስራ የሚያካሂደውን ወኪል እና ፀንቶ በሚሰራበት በኢትዮጵያ ወይም በሌላ አገር ህግ የተመሰረተ ወይም እውቅና ያገኘ

Ethiopia Region Income tax proclamation No. 19/2023;

4) **“Tax”** means Turnover Tax payable whenever transaction of sales of goods and services is carried out;

5) **“Gross Receipts”** means income, without reduction of expenses, including the cost of goods sold;

6) **“Taxable Transaction”** means a supply of goods or a rendition of services in the course or furtherance of a taxable activity, other than an exempt transaction described in Article 6 of this Proclamation;

7) **“A person not registered for VAT”** means a person who is not in compliance with the threshold set out in Article 12 of the VAT Proclamation No.1341/2024 or is below the amount determined by the Finance Bureau. Or a person who is not registered voluntarily due to failure to submit an application for registration under Article 13;

8) **“Body”** shall mean any company, registered partner ship, entity formed under foreign law resembling a company or registered partnership; or any public enterprise Or financial agency that carries out business activities including body of persons coroporate or unincorporated whether created or recognized under a law in force in

ቢሆንም ባይሆንም እንደድርጅት የሚንቀሳቀስን ይጨምራል፤

9) **“ዕቃ”** ማለት የልውውጥ ዋጋ ያለው ጠቀሜታ የሚሰጥ ወይም ፍላጎት የሚያሟላ ማናቸውም ዕቃ ወይም ሸቀጥ ሲሆን እንስሳትንም ይጨምራል፤

10) **“ሽያጭ”** ማለት ዕቃዎችን በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት መገበያየት እና የተወሰነ ክፍያ በመቀበል አገልግሎት መስጠት ሲሆን ታክስ ከፋዩ ያለክፍያ የሚሰጣቸውን ዕቃዎች ወይም የሚያቀርባቸውን አገልግሎት ይጨምራል፤

11) **“ታክስ ከፋይ”** ማለት የተርን ኦቨር ታክስን ሰብስቦ ለቢሮው ገቢ እንዲያደርግ ግዴታ የተጣለበት ሰው ነው፤

12) **“ኃላፊ”** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ሆኖ እንደአግባብነቱ በየአስተዳደር እርከኑ የሚገኙ መምሪያዎች ፤ጽ/ቤቶች እና የታክስ ማዕከላትን ሃላፊዎችን ነው፤

13) **“ሰው”** ማለት ማንኛውም ግለሰብ፣ ድርጅት ወይም ማኅበር ሲሆን ሌላ ሰውን በመወከል ተቀማጭነቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ የንግድ ስራ የሚያካሂድ የንግድ ወኪል ይጨምራል፤

**3. የአዋጁ ተፈፃሚነት**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 መሰረት ወይም ይህንን አዋጅ መሰረት በማድረግ በሚወጣዉ መመሪያ ነፃ ካልተደረጉ በስተቀር፣ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስት ለክልሉ መንግስት ተለይቶ በተሰጠ የግብር ስልጣን የሚካተቱ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገቡ ሰዎች በሀገር ውስጥ በሚሸጧቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ላይ በዚህ አዋጅ መሰረት ተርን ኦቨር ታክስ ይከፈላል።

Ethiopia or elsewhere, and any foreign body's business agent doing business in Ethiopia on behalf of the principal;

9) **“Goods”** means any type of goods or commodity that has exchange value, utility and brings about satisfaction, and includes animals;

10) **“Sale”** means exchange of goods in cash or in kind and rendering of services upon receipt of payment, and includes goods supplied or services rendered by the taxpayer free of charge;

11) **“Taxpayer”** means a person obliged to collect and transfer Turnover Tax to the Bureau;

12) **“Bureau head”** means the Head of the South Ethiopia Region Revenue Bureau and, as appropriate, the Heads of Departments, Offices and Tax Centers at each administrative level;

13) “**Person”** means any individual, organization or association, including a commercial agent domiciled in Ethiopia, who carries on business on behalf of another person;

**3.Scope**

Unless exempted under Article 7 of this Proclamation or directives to be issued thereunder, Turnover Tax shall be payable on goods supplied and services rendered by Persons not registered for Value Added Tax, which are specifically granted as a taxation power to the Regional Government by the Constitution

| | |
|---|---|
| | of the Federal Democratic Republic of Ethiopia. |
| **ክፍል ሁለት**<br>**የታክስ መክፈያ ልክ ስለመወሰንና ከታክስ ነፃ ስለማድረግ** | **SECTION TWO**<br>**The Rate of Tax and Exemption** |
| 4. **የተርን ኦቨር ታክስ ተመን**<br>1) በማናቸውም በአገር ውስጥ በሚሸጡ ዕቃዎች ላይ 2 ፐርሰንት (ሁለት በመቶ)፣<br>2) በአገር ውስጥ በሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ፣<br>ሀ/ የሥራ ተቋራጮች፣ የእህል ወፍጮ ቤቶች፣ የትራክተሮች እና ኮምባይን ሃርቨስተሮች አገልግሎት 2 በመቶ (ሁለት ፐርሰንት)<br>ለ/ ሌሎች10 በመቶ (አሥር ፐርሰንት) ተርን ኦቨር ታክስ ይከፍላሉ። | 4. **Rate of Turnover Tax**<br>The Turnover Tax shall be:<br>1) 2% (two percent) on Goods sold locally<br>2) for Services rendered locally;<br>a/ 2% (two percent) on Contractors, grain mills, tractors and combine-harvesters;<br>b/ 10% (ten percent) on others. |
| 5. **የተርን ኦቨር ታክስ ስሌት መሰረት**<br>ታክሱ የሚሰላበት ዋጋ የዕቃው ወይም የአገልግሎቱ ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ ነው። | 5. **Base of Computation of the Turnover Tax**<br>Base of computation of the Turnover Tax shall be the gross receipts in respect of goods supplied or services rendered. |
| 6. **የተርን ኦቨር ታክስ ሰብስቦ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት**<br>1) ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን የሚሸጥ ማናቸውም ሰው በሽያጩ ላይ ሊከፍል የሚገባውን ታክስ ከገዥው ሰብስቦ ለቢሮው ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት ። ስለሆነም ሻጩ ስለታክሱ የመጀመሪያ ተጠያቂ ይሆናል።<br>2) የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ማህበራት ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎችንና የአገልግሎቶችን ሽያጭ ሲያከናውኑ | 6. **Obligation to Collect and Transfer the Turnover Tax**<br>1) A person who sells goods nd services has the obligation to collect the Turnover Tax from the buyer arid transfers same to the Bureau. Hence, the seller is principally accountable for the payment of the tax.<br>2) Government agencies, non-governmental organizations, and associations are required to collect |

| | |
|---|---|
| የተርን ኦቨር ታክስን ከገዥው በመሰብሰብ ገቢ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡ በመሆኑም ሽያጩን ያከናወነው መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት ስለታክሱ የመጀመሪያ ተጠያቂ ይሆናል፡፡የታክሱ አሰባሰብና አፈጻጸም በደንብ ይወሰናል፡፡ | turnover tax from the purchaser when they sell taxable goods and services. Therefore, the agency or organization that made the sale is primarily responsible for the tax. The collection and implementation of the tax are well-defined. |
| 7. **ከታክስ ነፃ ስለመሆን** | **7. Exemption** |
| 1) የሚከተሉት ከተርን ኦቨር ታክስ ነፃ ይሆናሉ፡- | 1) The following shall be exempted from Turnover tax |
| ሀ/ ቢያንስ ለሁለት ዓመታት የገለገለ የመኖሪያ ቤት ሽያጭ እና የመኖሪያ ቤት ኪራይ፣ | a/the sale or transfer of a dwelling used for a minimum of two years, or the lease of a ; |
| ለ/የፋይናንስ አገልግሎቶች፣ | b/ the rendering of financial services; |
| ሐ/ ለሳንቲሞችና ሜዳልያዎች ጥናት አገልግሎት ከሚውሉት በስተቀር የአገር እና የውጭ ገንዘቦችን እና የዋስትና ሰነዶችን ማሰራጨት፣ | c/ the supply of national or foreign currency (except for that used for numismatic purposes) and of securities; |
| መ/ ሃይማኖት ድርጅቶች የሚሰጡ የእምነት ወይም ከአምልኮት ጋር የሚገናኙ አገልግሎቶች፣ | d/ the rendering by religious organizations of Religious or other related services; |
| ሠ/ የሕክምና አገልግሎት እና አግባብ ባለው የመንግስት መስሪያ ቤቶች በሚወጣ መመሪያ በሀኪም የሚታዘዙ መድሀኒቶች፣ በሌሎች እቃዎችና አገልግሎቶች ላይ የሚከፈለው ታክስ ቀሪ እንዲሆን ሊፈቀድ ይችላል፡፡ | e/ the supply of prescription drugs specified in directives issued by the relevant government agency, and the rendering of medical services; |
| ረ/ በትምህርት ተቋማት የሚሰጡ የማስተማር አገልግሎቶችን እንዲሁም ለህፃናት ጥበቃ በመዋዕለ ህፃናት የሚሰጡ አገልግሎቶች፣ | f/ the rendering of educational services provided by educational institutions, as well as child care services for children at pre-school institutions; |
| ሰ/ ለሰብአዊ እርዳታ የሚውሉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች፣ | g/ the supply of goods and rendering of services in the form of humanitarian aid; |
| ሸ/ የኤሌክትሪክ፣ የኬሮሲን እና የውሃ አቅርቦት፣ | h/ the supply of electricity, kerosene, and water; |
| ቀ/ የትራንስፖርት አቅርቦት፣ | i/ the provision of transport; |
| | j/ permits and license fees; |
| በ/ ማናቸውንም የስራ እንቅስቃሴ ለማከናወን ለሚሰጥ | k/ the supply of goods or services by a |

ፈቃድ ለመንግስት የሚፈፀም ክፍያ ፣

ተ/ ከ60% በላይ ሠራተኞቹ የአካል ጉዳተኛ በሆኑበት የአካል ጉዳተኞችን ቀጥሮ የሚሰራ ድርጅት የሚቀርባቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች፣

ቸ/ የመጻሕፍት አቅርቦት፣

2) በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴር ከታክስ ነፃ የሚያደርጋቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች በክልሉ ተፈፃሚነታቸው እንደተጠበቀ ሆነው የፋይናንስ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ በሌሎች ዕቃዎችና አገልግሎቶች የሚከፈለው ታክስ ቀሪ እንዲሆን ሊፈቅድ ይችላል፡፡

3) በዚህ አንቀፅ የተዘረዘሩት ከታክስ ነፃ የመሆን መብቶች አፈፃፀም ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የተርን ኦቨር ታክስ **አስተዳደር ሥርዓት**

### 8. ታክሱን **የማስተዳደር እና ሪፖርት የማቅረብ ኃላፊነት፡-**

1) በዚህ አዋጅ መሰረት የተርን ኦቨር ታክስን ስሌት በትክክል የማከናወን፣ የታክስን ማስታወቂያ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለቢሮ የማቅረብና ታክስን በጊዜው የመክፈል ኃላፊነት የታክስ ከፋዩ ነው፡፡

2) የተርን ኦቨር ታክስን የማስተዳደር ኃላፊነት የቢሮው ነው ፡፡

### 9. **የሂሳብ መዝገብ ስለመያዝ**

በክልሉ ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 19/ 2016 ድንጋጌ መሰረት የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የተጣለባቸው ታክስ ከፋዮች ለተርን ኦቨር ታክስ አወሳሰን እንዲያገለግል በገቢ ግብር አዋጅ የታዘዘውን የሂሳብ መዝገብ መያዝ አለባቸው፡፡

workshop employing disabled individuals if more than 60% of the employees are disabled; and

l/ the supply of books.

2) Subject to the Bureau granted by the Turnover Tax Proclamation to the Ministry of Finance, to exempt tax on goods and services, the Finance Bureau, may permit the tax payable on other goods and services to remain exempted in the region.

3) The implementation of the tax exemption rights listed in this article shall be determined by a directive issued by the Bureau.

## SECTION THREE

## **Administrative Procedures of** Turnover Tax

### 8. **Responsibility for tax administration and reporting:**

1) The responsibility for the correct calculation and timely payment of Turnover Tax and presentation of a return to the Bureau by the prescribed deadline rests on the tax payer in accordance with this Proclamation.

2) The Turnover Tax is administered by the Bureau.

### 9.Records

According to the provisions of the Regional Income Tax Proclamation No. 19/2023, taxpayers who are obliged to maintain accounting records shall keep the records prescribed by the Income Tax Proclamation for the purpose of determining Turnover Tax.

| | |
|---|---|
| **10.የተርን ኦቨር ታክስ ማስታወቂያ ስለማቅረብ እና ታክስን ስለማስከፈል** | **10. Filing of Turnover Tax Return and Payment** |
| **1) የተርን ኦቨር ታክስ ከፋዮች ግዴታ:-** | 1) Tax payers subject to Turnover Tax shall: |
| ሀ/ በቅይጥ ግብይት የተሰማራ ሆኖ በተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታ ያልተጣለበት የደረጃ «ሀ» ግብር ከፋይ የእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለቢሮው ወይም ቢሮው ለሚወክለው የፋይናንስ ተቋም ወይም በኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ዘዴ የተርን ኦቨር ታክስ ማስታወቂያ በማቅረብ መክፈል የሚገባውን ታክስ ወዲያውኑ የመክፈል፤ | a/ A category ”A” Tax payer, who involved in mixed transaction and not obliged to register to value added tax ,shall file a turnover Tax return and simultaneously pay to the Bureau or through electronics filing and payment system with in one month after the end of every accounting period. |
| ለ/ ታክሱ በሚከፈልበት የንግድ ስራ የተሰማራ የደረጃ «ሐ» ግብር ከፋይ በየዓመቱ የገቢ ግብሩን ሲከፍል አንድ ላይ ለቢሮው ወይም ቢሮው ለሚወክለው የፋይናንስ ተቋም የተርን ኦቨር ታክሱን በቁርጥ ስርዓት መሰረት የሂሳብ ጊዜው በተጠናቀቀ በአንድ ወር ውስጥ መከፈል የሚገባውን መጠን ወዲያውኑ የመክፈል፤ | b/ A category ”C” tax payer, who involve in taxable transaction, shall pay turn over tax with income tax payment with in one month after the end of fiscal year to the Bureau or to the financial institutions delegated by the revenue Bureau in standard system. |
| ሐ/ በቅይጥ አቅርቦት ሥራ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ታክሱን የሚሰበስበው ታክሱ በሚከፍልባቸው አቅርቦቶች ዋጋ ላይ ብቻ በመሆኑ የገቢ ማስታወቂያውን ይህንኑ በሚገልፅ ሁኔታ የማቅረብ፤ | c/ Aslong as a mixed supplier Collects tax only from the values of taxable supplies, he shall submit the income declaration in such a manner. |
| መ/ ታክስ ከፋዩ የተርን ኦቨር ታክስ ማስታወቂያ በሚያቀርብበት ወቅት በሂሳብ ጊዜው መከፈል ያለበትን ታክስ የመክፈል፤ | d/ A tax payer has an obligation to pay the tax while filing the turn over tax return. |
| ሠ/ የተርን ኦቨር ታክስ መሰብሰቢያ ደረሰኝ አጠቃቀም ግዴታ በተመለከተ በቅይጥ አቅርቦት ሥራ የተሰማራ ማንኛውም የተርን ኦቨር ታክስ ከፋይ በተመሳሳይ የቅይጥ አቅርቦት ስራ ላይ ተሰማርተው በተጨማሪ እሴት ታክስ ለተመዘገቡ አካላት በተዘረጋው አሰራር መሰረት መፈጸም አለባቸው። | e/ The usage of receipts of collect turn over tax for every body involved in mixed supply shall be governed by the system established for bodies that are involved in mixed supply and registered for VAT. |
| 2) **ለዚህ አንቀፅ አፈፃፀም «የሂሳብ ጊዜ» ማለት:-** | 2) For the purpose of this Article ‘accounting period’ shall mean; |
| ሀ/ በክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 19/ 2016 መሰረት የደረጃ «ሀ» ግብር ከፋዮች ተብለው የሚታወቁ እና ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታ የሌለባቸው ታክስ ከፋዮች በየወሩ፤ | a/ Persuant to Income tax proclamation No.19/2023, taxpayers who are laveled as category “A” and those who are obliged to register for VAT(value added tax). |
| ለ/ ለመንግስት መ/ቤቶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማሕበራት በየወሩ፤ | b/for Government Offices, Non Governmental Organizations,and Associations,every month. |
| ሐ./ በክልሉ ገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሰረት የሂሳብ መዝገብ ለሚይዙ የደረጃ «ለ» ግብር ከፋዮች በኢትዮጵያ የበጀት ዓመት ወይም በቢሮው ሲፈቀድ በአውሮጠ ዘመን አቀጣጠር ከዓመቱ የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ የሚቆጠር | c/ for category "B" taxpayers who are required to keep records under the Income tax proclamation of the Region, each three month period commencing from the first day of the Ethiopian fiscal year or when approved by the Bureau, the first day of the Gregorian |

| | |
|---|---|
| የየሶስት ወር ጊዜ፣<br>መ/ በገቢ ግብር በተደገነነው መሰረት የሂሳብ መዝገብ ለማይዙ የደረጃ «ሐ» ግብር ከፋዮች የበጀት ዓመቱ ነው፡፡ | calendar year;<br>d/ for Category "C" taxpayers, who are not required to keep records under Income Tax Proclamation, the fiscal year. |
| **11. የተርን ኦቨር ታክስ አወሳሰን** | **11. Assessment of the Tax** |
| 1) ቢሮው የታክስ ከፋዩን ሂሣብ ከመረመረ በኃላ ታክስ ከፋዩ ሊከፍል የሚገባውን ታክስ አሳንሶ ያስታወቀ መሆኑን የደረሰበት እንደሆነ ተጨማሪ የታክስ ውሳኔ ይሰጣል ፡፡ | 1) If, after review by the Bureau, it appears that a person has understated his tax obligation, the Bureau shall issue an additional assessment. |
| 2) የታክስ ከፋዩ የሂሣብ መዛግብትና ደጋፊ ሰነዶቹ በማናቸውም ምክንያት በቢሮው ዘንድ ተቀባይነት ካላገኙ ወይም በቢሮው እንዲቀርቡ ተጠይቆ ካልቀረቡ ወይም የሂሳብ መዛግብትና ደጋፊ ሰነዶች ከሌሉ ቢሮው ታክሱን ባለው መረጃ ወይም የዕቃውን ወይም የአገልግሎቱን የአገር ውስጥ ገበያ ዋጋ፣ ዋጋው የማይታወቅ ከሆነ የተመሳሳዩን የገበያ ዋጋ መሰረት በማድረግ ይወስናል ፡፡ | 2) If, for any reason, the books of account are unacceptable to the Bureau, or if the tax payer fails to submit same when requested by the Bureau, or if no books of account and supporting documents are maintained, the Bureau shall assess the tax on the basis of information available to it or on the basis of market price of such good or service in the local market or if the market price is unknown, on the basis of the market price of an equivalent good or service. |
| 3) በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሰረት የሂሳብ መዝገብ የማይዙ የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋዮች የተርን ኦቨር ታክስ በቁርጥ ይወሰናል ፡፡ በቁርጥ የሚወሰን የተርን ኦቨር ታክስ ስሌት መሰረት ለገቢ ግብር መሰረት የሆነው ጠቅላላ ገቢ ነው፡፡ | 3) A presumptive turnover tax shall be payable by Category "C" taxpayers who are not required to keep records. The base for the presumptive turnover tax shall be the total turnover used as base for the income tax. |
| 4) ቢሮው የሰጠውን የታክስ ውሣኔ በማስታወቂያ ተዘጋጅቶ ለታክስ ከፋዩ ይልካል፡፡ የውሣኔ ማስታወቂያ የመላኩ አፈፃፀም በታክስ አስተዳደር አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት ይፈፀማል፡፡ | 4) The assessment made shall be prepared in an assessment notification and be delivered to the tax payer. Delivery of the assessment notification shall be made in accordance with provisions of the Income Tax Proclamation. |
| 5) ቢሮው በንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ተጨማሪ የታክስ ውሳኔ የሰጠ እና የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ የደረሰው ሰው ማስታወቂያ በደረሰው በ30 ቀን ውስጥ እንዲከፍል የተጠየቀውን ተጨማሪ ታክስ ያልከፈለ ወይም በውሳኔው ላይ ቅሬታ ካለው በአንቀፅ 21 መሰረት | 5) If the Bureau makes an additional assessment under Sub-Article (1), and within 30 days of the notice and demand the person assessed does not pay the additional assessment or appeal the assessment as provided under Article 21, the person is in fault. |

ቅሬታ ያላቀረበ እንደሆነ ጥፋተኛ ነው፡፡

6) በዚህ አዋጅ አንቀፅ 8 መሰረት ታክስ ከፋዩ ታክሱን አስታውቆ ከከፈለበት በጀት ዓመት መጨረሻ አንስቶ በ3 ዓመት ጊዜ ውስጥ ቢሮው የታክስን ልክ ወስኖ ቀሪ ሂሳብ መኖሩን ካላስታወቀ የተከፈለው ታክስ በቂና የመጨረሻ ይሆናል ፡፡ ሆኖም ታክስ ከፋዩ ገቢውን ያላስታወቀ ወይም የተጭበረበረ የገቢ ማስታወቂያ ያቀረበ እንደሆነ ቢሮው በማናቸውም ሌላ ህግ የተደነገገው ይርጋ ሳያግደው ታክስን በማናቸውም ጊዜ መወሰን ይችላል ፡፡ ይህ ድንጋጌ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታ የሌለባቸው ደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች በተመለከተ ሲሆን በአምስት ኣመት ጊዜ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት
## የታክስ አሰባሰብ አፈፃፀም

### 12. የገቢዎች ቢሮ ስልጣንና ተግባር

በዚህ አዋጅ እና በሌሎች ህጎች ከተጠቀሱት በተጨማሪ ቢሮው የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

1) ይህን አዋጅ በሥራ ላይ የማዋል እና የማስፈፀም፤
2) በማናቸውም ሌላ ህግ ውስጥ ተቃራኒ የሆኑ ድንጋጌዎች ቢኖሩም፣ቢሮው በማናቸውም ጊዜ በታክስ ከፋዩ የቀረቡ ማናቸውንም መግለጫዎች፣ ሰነዶችና የሂሳብ መዝገቦች ለማረጋገጥ፣

   ሀ/ ህጋዊ ሥልጣን የተሰጣቸውን ተቆጣጣሪዎች ወደ ታክስ ከፋዩ የንግድ ወይም የሙያ ሥራ ቦታ በመላክ የሂሳብ መግለጫዎችን፣ ሰነዶችን እና የሂሳብ መዝገቦችን ወይም ገቢና ወጪን የሚያሳዩ ሰነዶችን ለንግድ የተከማቹ ዕቃዎችን ወይም ሌሎች ዕቃዎችን ለማመሳከርና ለመመርመር፣

6) If the Bureau fails to assess the tax and notify the taxpayer of the amount still due within three years from the date of declaration and payment of the tax by the taxpayer in accordance with Article 8 of this Proclamation, the tax so paid shall be final and conclusive. In case where the taxpayer has not declared his income or has submitted a fraudulent declaration, no time limit provided in any other law shall bar· the assessment of the tax by the Bureau. This provision applies to Category "A" taxpayers who are not required to register for VAT and will be effective for a period of five years.

## SECTION FOUR
## Collection Enforcement

### 12.Powers and Functions of the Bureau

In addition to the powers vested in it in other provisions of this Proclamation, the Bureau shall have the following powers and duties:

1) To implement and enforce this Proclamation:
2) Notwithstanding contrary provisions in any other law, the Bureau shall be empowered to investigate any statements, records and books of account submitted by any taxpayer at any time by:

   a/ sending duly accredited inspectors to check the statements, records and books of account, or any vouchers, stocks or other material items at the person's place of business or practice;

   b/ requiring the person or any employee

ለ/ ታክስ ከፋዩን ወይንም የሂሳብ መዝገቦቹን እና ሰነዶችን ወይም መረጃን ለማግኘት የሚችለውን ወይንም እነዚህን የመጠበቅ ኃላፊነት የተሰጠውን ማንኛውንም የታክስ ከፋዩን ተቀጣሪ በአመቺ የቢሮው የሥራ ሰዓቶች እና ጽ/ቤት ተገኝቶ ለሚቀርቡለት ለጉዳዩ አግባብ ያላቸው ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጥና የተባሉትንም ሰነዶች እንዲያቀርብ ለማድረግ፣

ሐ/ ማዘጋጃ ቤት፣ ፋይናንስ ተቋም ወይም ማንኛውም የፌደራል ወይም የክልል መንግስት መሥርያ ቤት ጨምሮ ማንኛውም ሰው ስለታክስ ከፋዩ የሚያውቀውን መረጃ ወይም የሥራ እንቅስቃሴ ዝርዝር እንዲገልፅ ለማድረግ ይችላል፡፡

who has access to or custody of any information, records or books of account to produce the same and to attend during normal office hours at any reasonably convenient tax office and answer any questions relating thereto;

c/requiring any person including a municipality, financial institution, or Federal or Regional Government offices to disclose particulars of any information or transactions relating to a certain taxpayer.

## 13. ታክስ ለመሰብሰብ ሀብት ስለመያዝ

1) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም በዚህ አዋጅ የተጣለው ታክስ የሚፈለግበት ሰው በአንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 5 ወይም በአንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው መሰረት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ቢሮው የዚህን ታክስ ከፋይ ሀብት በመያዝ ለሚፈለግበት ታክስ እና ንብረቱን ለመያዝ የተደረገውን ተጨማሪ ወጪ ለመሸፈን እንዲውል ለማድረግ ህጋዊ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

2) ለዚህ ክፍል አፈፃፀም “መያዝ” በማናቸውም መንገድ መያዝን፣ እንዲሁም የተርን ኦቨር ታክስ የሚፈለግበት ሰው የሆነ ገንዘብ ወይም ንብረት በእጅ ከሚገኝ ሰው ታክስ መሰብሰብን ይጨምራል፡፡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 እና 6 በተነገረው መሰረት ካልሆነ በስተቀር መያዝ የሚቻለው የመያዝ ትዕዛዝ በተሰጠበት ጊዜ በይዞታ ሥር የሚገኝ ንብረት እና የመያዝ ተግባር በሚከናወንበት ጊዜ ፀንቶ ያለ ግዴታን በተመለከተ ብቻ ነው፡፡ ቢሮው የታክስ ከፋዩን ሀብት በሚይዝበት ጊዜ

## 13. Seizure of Property to Collect Tax

1) Subject to Sub-Article (4) of this artcle, if any person liable to pay any tax imposed by this Proclamation is in default under Sub-Article (5) of Article 11 or Sub--Article (2) of Article 21, it shall be lawful for the Bureau to collect such tax and such further amount as shall be sufficient to cover the expense of the seizure by seizing property belonging to such person.

２) For the purposes of this Section, the term "seizure" includes seizure by any means, as well as collection from a person who owes money or property to the person liable for Turnover Tax. Except as provided in Sub-Article (3) and (6), a seizure shall extend only to property possessed by and obligations owed to the taxpayer existing at the time the seizure is made. The Bureau may request the attendance of a police officer during the seizure. Where the Bureau seizes any property as

| | |
|---|---|
| የፖሊስ ሠራዊት አባል እንዲገኝ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ቢሮው ከዚህ በላይ በተመለከተው መሰረት ሀብቱን ከያዘበት ቀን አንስቶ ከሚቆጠር ከ10 (አሥር) ቀናት ጊዜ በኋላ በሐራጅ ወይም በቢሮው በተፈቀደ በማናቸውም ሌላ ዘዴ የያዘውን ንብረት መሸጥ ይችላል፡፡ ሆኖም ንብረቱ የሚበላሽ ከሆነ የንብረቱን ባህርይ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተገቢ መስሎ በሚታየው ጊዜ ሊሸጠው ይችላል፡፡ | provided herein above. it shall have the right to sell the seized goods at public auction or in any other manner approved by the Bureau not Jess than l0 days after the seizure, except that when the goods seized are perishable. the Bureau can sell the goods after any reasonable period having regard to the nature of the goods. |
| 3) ማናቸውም የተያዘ ንብረት ለመያዝ ምክንያት የሆነውን የታክስ ዕዳ ለመሸፈን በቂ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ ቢሮው ከታክስ ከፋዩ ላይ የሚፈለገው የታክስ ዕዳ እና ከዚህ ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ ወጪዎች ተከፍለው እስከሚጠናቀቁ ድረስ የታክስ ዕዳው የሚፈለግበትን ሰው ሌሎች ሀብቶች መያዝ ይችላል ፡፡ | 3) Whenever any property on which seizure had been made is not sufficient to satisfy the claim for which seizure is made, the Bureau may, there after and as may be necessary, proceed to seize other property liable to seizure of the person against whom the claim exists until the amount due from such person, together with all expenses, is fully paid. |
| 4) ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ1 በተደነገገው መሰረት ባልተከፈለ የታክስ ዕዳ ምክንያት ንብረት መያዝ የሚቻለው ቢሮው ሃብቱን የመያዝ ሃሳብ እንዳለው አስቀድሞ ለታክስ ከፋዩ በፅሁፍ ካስታወቀው በኋላ ይሆናል፡፡ በዚህ አይነት የሚሰጠው ማስታወቂያ ሃብቱ ከመያዙ ከ30 ቀን በፊት ለታክስ ከፋዩ ሊደርሰው ይገባል፡፡ | 4) Seizure under Sub-Article (1) on property of any person in default with respect to any unpaid tax may be made only after the Bureau has notified such person in writing of the intention to make such seizure. The notice shall be delivered not less than thirty 30 (thirty) days before the day of the seizure. |
| 5) ቢሮው የታክስ አሰባሰብ የሚያደናቅፍ ሁኔታ መኖሩን የተረዳ እንደሆነና በንዑስ አንቀጽ1 የተመለከተ የ30 ቀን የጊዜ ገደብ እና በንዑስ አንቀጽ 4 የተመለከተው የ30 ቀን ጊዜ ገደብ ሳይጠበቅ ታክስ ወዲያውኑ እንዲከፈል ለማድረግ ጥያቄ ካቀረበ እንዲሁም ታክስ ከፋዩ ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ ንብረትን በመያዝ ታክስ የመሰብሰቡ አፈፃፀም ህጋዊ ይሆናል፡፡ | 5) If the Bureau makes a finding that the collection of the tax is in jeopardy and demanded for immediate payment of such tax (without regard to the 30 days period) provided in Sub-Article (1) and (4) upon failure or refusal of the taxpayer to pay such tax, collection of the tax by seizure of property before such period shall be lawful. |
| 6) ማናቸውም ንብረት የተያዘ ወይም እንዲያዝ የታሰበ ከሆነ ስለዚሁ ንብረት ማስረጃ የሚሆን ወይም መግለጫ የያዘ ሰነድ ወይም መዝገብ በእጁ የሚገኝ ወይም በቁጥጥሩ ሥር ያለ ማናቸውም ሰው | 6) If a seizure has been made or *is* about to be made on any property, any person having custody or control of any books or records containing evidence or statements |

| | |
|---|---|
| በቢሮው ጥያቄ ሲቀርብለት ሰነዱን ወይም መዝገቡን ለማስረጃነት ማቅረብ አለበት ፡፡ | relating to the property subject to seizure shall, on demand, exhibit such books or records to the Bureau. |
| 7) በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተከበረ ወይም በአፈፃፀም ላይ ያለ ወይም በዋስትና የተያዘ ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም በታክስ ምክንያት የተያዘ ንብረት በእጁ የሚገኝ ወይም ለታክስ ከፋዩ ማናቸውም ግዴታ ያለበት ሰው ቢሮው ሲጠይቀው የያዘውን ሃብት ለቢሮ የማስረከብ ወይም ያለበትን ግዴታ የመፈጸም ኃላፊነት አለበት፡፡ | 7) Unless the property is attached by a court order or is in execution, or is held on security, any person who has any property seized for tax purposes or who owes any duty to the taxpayer shall be responsible for delivering the property to the Bureau or fulfilling the duty owed to him upon request by the Bureau. |
| 8) ማናቸውም ሰው ቢሮው ሲጠይቀው አንድን የተያዘ ንብረት ለማስረከብ ፍቃደኛ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ በተያዘው ንብረት መጠን በግል ተጠያቂ ይሆናል፡፡ ሆኖም ተጠያቂነቱ ለንብረቱ መያዝ ምክንያት ከሆነው የታክስ ዕዳ መጠን ወይም በታክስ ዕዳ ላይ የሚታሰበውን ወጪ እና ወለድ ጨምሮ ሊያልፍ አይችልም፡፡ | 8) Any person who fails or refuses to surrender any property subject to seizure, when demanded by the Bureau, shall be personally liable to the government in a sum equal to the value of the property not so surrendered, but not exceeding the amount of tax for the collection of which seizure has been sought (together with costs and interest on such sum). |
| 9) በንዑስ አንቀጽ 8 ከተመለከተው የግል ተጠያቂነት በተጨማሪ ንብረቱን የያዘው ሰው ንብረቱን ለማስረከብ ፍቃደኛ ያልሆነው ያለበቂ ምክንያት ከሆነ በንዑስ አንቀጽ 8 መሰረት የሚፈለገውን የገንዘብ መጠን 50 ፐርሰንት(ሃምሳ በመቶ) በተጨማሪ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ | 9) In addition to the personal liability imposed by Sub-Article (8), if the failure or refusal to surrender is without reasonable cause, such person shall be liable for an additional charge equal to fifty per cent (50%) of the amount recoverable under Sub-Article (8). |
| 10) በዚህ አንቀጽ መሰረት በይዞታው ሥር ያለውን ንብረት ያስረከበ ወይም በታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ገንዘብ ከቢሮው በተጠየቀው መሰረት ገቢ ያደረገ ማናቸውም ሰው ካስረከበው ንብረት ወይም ገቢ ካደረገው ገንዘብ ጋር በተያያዘ የታክስ ግዴታውን ባልተወጣው ታክስ ከፋይ ወይም ማናቸውም ሌላ ሰው ከሚፈልግበት ዕዳ ወይም ካለበት ግዴታ ነፃ ይሆናል፡፡ | 10) Any person in possession of the property of a taxpayer in default and who surrenders such property or pays the tax in accordance with this Article to which the owner is liable, shall be discharged from any obligation or liability to the delinquent or to any other person arising from such surrender or payment. |
| **14. በሀብት ላይ የሚቀርብ የቀደምትነት መብት ጥያቄ** | **14. Preferential Claim to Assets** |
| 1) ዋስትና የተሰጣቸው የሌሎች አበዳሪዎች የቅድሚያ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ አዋጅ መሰረት ታክስ ተከፋይ ከሚሆንበት | 1) Subject to the prior secured claims of creditors, the Bureau has a preferential claim upon the assets of the person liable to pay the tax until |

ቀን አንስቶ ተከፍሎ እስከ አለቀበት ጊዜ ድረስ ታክስ የመክፈል ግዴታ ባለበት ሰው ሃብት ላይ ቢሮው የቀደምትነት መብት ይኖረዋል፡፡

2) ማናቸውም ሰው ታክስ የመክፈል ግዴታውን ባለመወጣት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ቢሮው በጥፋት ምክንያት ያልተከፈለው ታክስ እና ታክስን ለማስከፈል የሚደረገውን እንቅስቃሴ የሚያስከትለውን ወጪ ማስከፈል እንዲቻል የታክስ ዕዳ የሚፈለግበትን ሰው ሀብት በዋስትና ተይዞ እንዲቆይ ንብረቱን ለመዘገበው አካል የፅሑፍ ትዕዛዝ የሚሰጥ መሆኑን የሚገልጽ ማስጠንቀቂያ ለተመዘገበው ሰው ይሰጣል፡፡

3) በንዑስ አንቀጽ 2 የተገለፀው ማስጠንቀቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ ማስጠንቀቂያው በደረሰው በ30 ቀን ውስጥ ታክስን ያልከፈለ እንደሆነ ቢሮው ለንብረት መዝጋቢው ቢሮ የተመዘገበው ሰው ሀብት ባልተከፈለው የታክስ ዕዳ መጠን በዋስትና ተይዞ እንዲቆይ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

4) በንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ቢሮው ታክስ የሚፈለግበት ሰው ሃብት በዋስትና ተይዞ እንዲቆይ ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን፣ መዝጋቢው ቢሮ ማናቸውንም ክፍያ ሳይጠይቅ ንብረቱ በዋስትና እንዲያዝ የደረሰውን ትዕዛዝ እንደማናቸውም በሀብቱ ላይ እንዳለ የመያዝ ሰነድ ይመዘግባል፡፡ ቀደም ሲል የተሰጠ የመያዝ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዋስትናው ምዝገባ የሚፈለገውን ታክስ ለማስከፈል በማናቸውም መልኩ በህግ እንደተሰጠ መያዣ ወይም እንደማናቸውም ሌላ ዕዳ ወይም ክፍያ ሆኖ ይቆጠራል፡፡

## 15. ታክስ ከፋዩ ስላለው ጥበቃ

በዚህ ክፍል መሰረት የተያዘ ማናቸውም ንብረት የሚያዘው፣ የሚጠበቀው፣ እና የሚመዘገበውን የመንግስት አካል በዚህ ክፍል መሰረት የተያዘውን ንብረት በማናቸውንም ሌላ ምክንያት መሰረት

the tax is paid from the date on which tax becomes due and payable under this Proclamation.

2) Where a person is in default of paying tax, the Bureau may, by notice in writing, inform that person of the Bureau's intention to apply to the Registering Bureau to register a security interest in any asset which is owned by that person, to cover any unpaid tax together with any expense incurred in recovery proceedings.

3) If the person on whom a notice has been served under Sub Article (2) fails to pay the amount specified in the notice within 30 days after the date of service, the Bureau may, by notice in writing, direct the Registering Bureau that the asset, to the extent of the defaulter's interest therein, shall be the subject of security for the total amount of unpaid tax.

4) Where the Bureau has served a notice on the Registering Bureau under Sub-Article (3), the Registering Bureau shall, without fee, register the notice of security as if the notice were an instrument of mortgage over or charge on, as the case may be, such asset, and such registration shall, subject to any prior mortgage or charge, operate while it subsists in all respects as a legal mortgage over or charge on the asset to secure the amount.

## 15.Tax Taxpayer's Safeguards

Any property seized under this Section shall be seized, held, and accounted for only by the Bureau. No other agency of the government may require the property seized to be transferred or given over to it

በማድረግ እንዲሰጠው ወይም እንዲተላለፍለት መጠየቅ አይችልም፡፡ የተያዘ ንብረት የተሸጠ እንደሆነ ከሽያጭ ከተገኘው ገንዘብ ውስጥ ታክስ ከፋዩ ከሚፈለግበት ዕዳ በላይ የሆነው ገንዘብ ለንብረት ባለቤት ወዲያውኑ ይመለሳል፡፡

## 16. የተረካቢ ግዴታ

1) በዚህ አንቀጽ ውስጥ "ተረካቢ" ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የታክስ ከፋዮን ሀብት በተመለከተ፡-

ሀ/ የኩባንያ የንብረት አጣሪ ሆኖ የተሰየመ፣
ለ/ ከፍርድ ቤት ውጪ ወይም በፍርድ ቤት የተሾመ ተረካቢ፣
ሐ/ በኪሣራ ውስጥ የሚገኝ ድርጅት ባለአደራ፣
መ/ የሞተን ሰው ንብረት የሚያስተዳድር፣ ወይም
ሠ/ በህግ ችሎታ የሌለውን ሰው ንግድ ሥራ የሚያካሂድ፣ ማናቸውም ሰው ነው፡፡

2) በኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ንብረት ተረካቢ ሆኖ የተሾመ ወይም ንብረት በይዞታው ሥር የተደረገ ተረካቢ ከተሾመበት ወይም ንብረቱ በይዞታው ሥር ከተደረገበት ከሁለቱ ከቀደመው ቀን ጀምሮ በ14 ቀን ጊዜ ውስጥ የተሾመ ወይም ንብረት በይዞታው ሥር ያለ መሆኑን ለቢሮ ማስታወቅ አለበት፡፡

3) ቢሮው ንብረቱ በተረካቢው ይዞታ ሥር ያለ ሰው የሚፈለግበትን የታክስ ዕዳ ለመሸፈን የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን ለተረካቢው በጽሑፍ ያስታውቃል፡፡

4) ተረካቢ፡-

ሀ/ በንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በቢሮው የተገለፀውን የገንዘብ መጠን ወይም ከማስታወቂያው በኃላ በስምምነት የተደረሰበትን ሌላ የገንዘብ መጠን ከንብረቱ ሽያጭ ላይ

for any cause whatsoever. If any property seized is sold, any portion of the proceeds in excess of the person's liabilities shall be returned promptly to the owner.

## 16. Duties of Receivers

1) In this Article "receiver" means a person who, with respect to an asset in Ethiopia of a registered person, is:

a/ a liquidator of a company;
b/ a receiver appointed out of court or by a court;
c / a trustee for an un rehabilitated insolvent;
d/a mortgagee in possession;
e/ an executor of a deceased's estate; or
f/ any other person conducting a business on behalf of a person legally incapacitated.

2) A receiver shall notify, in writing, his appointment or his possession to the Bureau within 14 days after having been appointed to the position or taken possession of an asset in Ethiopia, whichever first occurs.

3) The Bureau may, in writing, notify a receiver, of **the** amount which appears to the Bureau to be sufficient to provide for tax which is or will become payable by the person whose assets are in the possession of the receiver.

4) A receiver;

a/ shall set aside, out of the proceeds of sale of an asset, the amount specified by the Bureau under Sub-Article (3), or such a lesser amount as is subsequently agreed on by the Bureau ;

ቀንሶ ለብቻው ያስቀምጣል፡፡

ለ/ ተቀንሶ ለብቻው በተቀመጠው የገንዘብ መጠን ልክ የተረከበው ንብረት ባለቤት ከሆነው ሰው ለሚፈለገው የታክስ ዕዳ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

ሐ/ በዚህ አንቀጽ የተመከተው ቢኖርም ከታክስ ቀደምትነት ያለው ማናቸውም ዕዳ ሊከፍል ይችላል።

5) ተረካቢው በንዑስ አንቀፅ 3 የተጠቀሰውን ታክስ በተመለከተ በንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት ተቀንሶ ለብቻው እንዲቀመጥ የተደረገውን የገንዘብ መጠን በዚህ አንቀጽ ለተጠቀሰው ታክስ ካላዋለ ተቀንሶ ለብቻው በተቀመጠው ገንዘብ ልክ በግል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 17. ለውጦች ስለማስታወቅ

ማናቸውም ታክስ ከፋይ፡-

1) ስሙ፣አድራሻው፣ንግድ ሥራው ቦታ፣ አደራጃጀቱ፣ ወይም ታክስ የሚከፈልበትን ዋንኛው የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ወይም የሚያከናውናቸውን ተግባራት ዓይነት፣

2) ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚከናወንበትን አድራሻ ወይም ስም የቀየረ እንደሆነ ይህንኑ ለቢሮው በ30 ቀናት ውስጥ ማስታወቅ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## ይግባኝ የሚቀርብበት ሥርዓት

## 18. የአቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል

የአቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል በቢሮው እንደአግባብነቱ በዞን፣ በወረዳ፣ በከተማ አስተዳደር በሚገኙ የቢሮው መዋቅር ይቋቋማል፡፡

b/ is liable to the extent of the amount set aside for the tax of the person who owned the asset; and

c/ may notwithstanding any provision of this Article pay any debt that has priority over the tax referred to in this Article.

5) A receiver is personally liable to the extent of any amount required to be set aside under Sub-Article (4) for the tax ·referred to in Sub-Article (3) if, the receiver fails to comply with the requirements of this Article.

## 17.Notification of Changes

A registered taxpayer shall notify the Bureau , in writing, of:

1) Any change in the name, address, place of business, constitution, or nature of the principal taxable activity or activities of the person; and
2) Any change of address from which, or name in which, a taxable activity is carried on by the registered person, within 21 days following such change.

## SECTION FIVE

## Appeal Procedure

## 18.Review Department

Members of the Review department shall be appointed by the Bureau of the Revenue, and as appropriate, upon the recommendation of the head of the Bureau.

| | |
|---|---|
| **19.የአቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል ስለሚኖረው ሥልጣንና ተግባር፡-**<br>1) ተጠሪነቱ ለቢሮ ሆኖ፡-<br>ሀ/ የታክስ ግዴታ እንዲሻሻል ፣የታክስ ከፋዮች መቀጫ እንዲነሳ የሚቀርቡ ማመልካቻዎችን ለመመርመርና ውሳኔ ለመስጠት፣<br>ለ/ ከቀረቡት አቤቱታዎች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ማናቸውንም የጽሑፍ ማስረጃዎች ወይም ሰነዶች መሰብሰብ፣<br>ሐ/ በምርምራ ላይ የሚገኘውን ጉዳይ በሚመለከት ረገድ ቀርቦ የሚጠየቀውን ጥያቄ እንዲመልስ ከታክስ አወሳሰን ጋር በቀጥታ ወይም ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ግንኙነት ያለውን ማንኛውንም ሰው የመጥራት፣<br>መ/ ቢሮው የሰጠው የታክስ ውሳኔ ትክክለኛ፣ የተሟላ እና ይህንን አዋጅ ጠብቆ የተሰጠ መሆኑን የማረጋገጥ ስልጣን ይኖረዋል፡፡ | **19.Powers and Duties of the Review Department**<br>1) The Review Department shall be accountable to the head of the Bureau and shall have the following duties:<br>a/ to examine and decide on all applications submitted by tax payers for compromise of penalty, interest and on the tax assessed;<br>b/ to gather any written evidence or information relevant to the matter submitted to it;<br>c/ to summon any person who directly or indirectly has dealt with the assessment, to appear before it to answer questions about the case under its investigation ;and<br>d/ to review the accuracy, completeness, and compliance with this Proclamation of the tax assessment made by the Bureau. |
| 2) የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ከታክስ ከፋዮች የሚቀርበውን አቤቱታ ሊያይ የሚችለው ታክስ ከፋዩ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ21 ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ካቀረበ ነው፡፡<br>3) ቢሮ ኃላፊው የኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ ሊያጸድቀው ወይም በውሳኔ ሀሳቡ ካልተስማማ ምክንያቱን በመግለጽ ጉዳዩ እንደገና እንዲያይ ለኮሚቴው ሊመልሰው ይችላል፡፡ | 2) The Department shall only review applications submitted to it within 10 days of receipt of tax assessment notification.<br>3) The Head of the Bureau may approve the recommendations or remand the case, with his observations, to the Department for further review. |
| **20. መቀጫን ስለማንሳት**<br>1) ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በታክስ ከፋይ ላይ የተጣለ አስተዳደራዊ መቀጫ በሙሉ፣ ወይም በከፊል እንዲነሳ ለማድረግ ይችላል፡፡ | **20.Waiver of Penalty**<br>1) The Review Department may waive administrative penalties, wholly or partly, in accordance with the directives to be issued by the Minister of Revenue or by the competent Bureau of the regional government, as may be appropriate. |

| | |
|---|---|
| 2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት የሚነሳው መቀጫ በአዋጁ አንቀፅ 4 መሰረት የሚታሰበውን ወለድ አይጨምርም፡፡ | 2) The administrative penalties wavied under sub Article 1 of this Article shall not include the interest prescribed under Article 4 of this proclamation. |
| **21. ይግባኝ** | **21.Appeal** |
| 1) በቢሮው የተላለፈውን የተጨማሪ ታክስ ውሳኔ የሚቃወም ማናቸውም ታክስ ከፋይ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ከደረሰው ወይም በአቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ30 /ሰላሳ/ ቀናት ውስጥ በቢሮው የተወሰነውን ተጨማሪ ታክስ 50% /ሃምሳ በመቶ/ ለቢሮው በማስያዝ ለይግባኝ ሰሚ ኮሚሽን ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡ | 1) Any person who objects to an additionalመ assessment made by the Bureau has the right to appeal, within 30 days from the receipt of assessment notification, or from the date of decision of the Review Committee, to the Tax Appeal Commission by depositing in cash with the Bureau 50% (fifty percent) of the additional tax assessed. |
| 2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ይግባኝ ቀርቦ የግብር ይግባኝ ኮሚሽን ታክስ ከፋዩ በተጨማሪ የተወሰነበትን ታክስ በሙሉ ወይም በከፍል የመክፈል ግዴታ እንዳለበት ውሳኔ ከሰጠበት ቀን አንስቶ በ30/ሰላሳ/ ቀን ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ተጨማሪ ታክስ ካልከፈለ ወይም ይግባኝ ካልጠየቀ ጥፋተኛ ነው፡፡ | 2) If a person appeals in accordance with Sub-Article (1) and the Tax Appeal Commission determines that the person is liable for the additional assessment, he shall be in default unless he pays the additional assessment determined by the Tax Appeal Commission within thirty (30) days of the rendition of such a decision. |
| 3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተ ጊዜ ውስጥ ይግባኝ ካልቀረበ በቢሮው የተወሰነው ተጨማሪ ታክስ ትክክለኛና የመጨረሻ ሆኖ ወዲያውኑ ተከፋይ ይሆናል፡፡ | 3) If no appeal is made within the period prescribed in Sub-Article (1) of this Article, the Additional assessment of the tax made by the Bureau shall be deemed to be correct and final, and shall be immediately payable. |
| 4) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በክልሉ ታክስ አስተዳደር አዋጅ ስለይግባኝ የተደነገጉ አንቀፆች እንደአግባብነታቸው በዚህ አዋጅ መሰረት የተወሰኑ ታክሶችን በሚመለከት ለሚቀርቡ ይግባኞች ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ | 4) Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the provisions of the Income Tax Proclamation relating to appeals shall, mutatis mutandis, apply to appeals regarding taxes imposed by this Proclamation. |
| **22. የማስረዳት ሸክም** | **22. Burden of Proof** |
| የተወሰነው ግብር በዝቷል ወይም ቢሮው የሰጠው ውሳኔ | The burden of proving that an assessment is |

ትክክል አይደለም በሚል በሚቀርብ ክርክር የማስረዳቱ ሸክም የተወሰነውን ታክስ ወይም የቢሮውን ውሳኔ የሚቃወም ሰው ይሆናል፡፡

## ክፍል ስድስት

## አስተዳደራዊ ቅጣቶች

### 23. የታክስ ማስታወቂያን በጊዜ ባለማቅረብ ስለሚፈፀም ቅጣት

1) በዚህ አዋጅ በሌላ አኳኋን እንዲፈጸም ከተወሰነው በስተቀር፣ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የታክስ ማስታወቂያ ግዴታውን ያልተወጣ ታክስ ከፋይ ለዘገየበት ለእያንዳንደ ወር ወይም የወሩ ከፊል ለሆነው ጊዜ፣ ያልተከፈለውን ታክስ 5% /አምስት በመቶ/፣25% /ሃያ አምስት ፐርሰንት/ እስኪሞላ ድረስ መቀጫ ይከፍላል፡፡

2) የታክስ ማስታወቂያ መቅረብ ባለበት ወር ወይም የወሩ ከፊል በሆነው ጊዜ የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ መሰረት የሚከፈለው መቀጫ ከብር 50,000 /ሃምሳ ሺህ/ አይበልጥም፡፡

3) ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ያልተከፈለ ታክስ ነው የሚባለው በታክስ ማስታወቂያ ላይ መታየት በነበረበት እና ታክስ መከፈል ባለበት ቀን በተከፈለው ታክስ መካከል ያለው ልዩነት ነው፡፡

4) በማናቸውም ሁኔታ የሚጣለው ቅጣት ቀጥሎ ከተመለከቱት ከዝቅተኛው ያነሰ አይሆንም፣

   ሀ/ ብር 10,000 ሺህ/አሥር ሺህ ብር/

   ለ/ በታክስ ማስታወቂያ ላይ መመልከት ከነበረበት የታክስ መጠን 100% (አንድ መቶ ፐርሰን) ፣

excessive or that a decision of the Bureau is wrong is on the person objecting to the assessment or decision.

## SECTION SIX

## Administrative Penalties

### *23.*Penalties for Late Filing

1) Except as otherwise provided in this Proclamation, a taxpayer who fails to pay his tax obligation within such period shall pay a penalty of 5% (five hundred) of the unpaid tax, up to a maximum of 25% (twenty-five per cent) for each month or part thereof that the taxpayer is late in paying the tax.The penalty under Sub-Article (1) of this Article is limited to 50,000 Birr for the first month (or portion thereof) in which no return is filed.

2) A person who fails to file a tax return during the month or part of the month in which the tax return is due shall be subject to a fine not exceeding Birr 50,000 (fifty thousand) in accordance with the provisions of Sub-Article /1/ of this Article.

3) For the purposes of this Article, unpaid tax is the difference between the tax that should have been shown on the tax notice and the tax that was paid on the date the tax was due.

4) In any event the penalty may not be less than the smaller of the two amounts:

   a/10,000 birr (ten thousand Birr);

   b/100 %( hundred percent) of the amount of tax required to be shown on the return.

**24. ዘግይቶ በተከፈለ ታክስ ላይ ስለሚታሰብ ወለድ**

1) መከፈል በነበረበት ጊዜ ላልተከፈለ ታክስ፣ መክፈል ከነበረበት ቀን እስከተከፈለበት ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ ወለድ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሰረት የሚከፈለው ወለድ የማስከፈያ ልክ ባለፈው የሩብ ዓመት በንግድ ባንኮች ሥራ ላይ በዋለው ከፍተኛው የማበደሪያ ወለድ ምጣኔ ላይ 15% /አስራ አምስት በመቶ/ ታክሎበት ይሆናል፡፡

## ክፍል ሰባት

## የወንጀል ቅጣቶች

**25. በታክስ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ስለሚመሩበት ሥነ-ሥርዓት**

በዚህ ክፍል የተዘረዘሩት በታክስ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች የወንጀል ህጉን ወይም በክልሉ የታክስ አስተዳደር አዋጅ የታክስ ወንጀሎች ተብሎ የተደነገጉትን በመተላለፍ የሚፈፀሙ በመሆኑ ክስ የሚመሠረተው፣ የሚታየው እና ይግባኝ የሚቀርበው በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓት መሠረት ይሆናል፡፡

**26. ህግን በመጣስ ታክስ ስላለመክፈል**

የሰበሰበውን ታክስ ያላስታወቀ ወይም የሚፈለግበትን ታክስ ያልከፈለ ማናቸውም ሰው ወንጀል እንደፈፀመ ይቆጠራል፡፡ ስለሆነም በዚህ አዋጅ ክፍል ስድስት መሠረት ከሚጣልበት መቀጫ በተጨማሪ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ አግባብ ባለው የወንጀል ህግ ከ5 ዓመት በማያንስ እሥራት ይቀጣል፡፡

**27.የሐሰት ወይም አሳሳች መረጃ ስለማቅረብ**

1) ማናቸውም ታክስ ከፋይ፡-

ሀ/ ለቢሮ ሠራተኛ አንድን ነጥብ በተመለከተ የሀሰት

**24.Late Payment Interest**

1) If any amount of tax is not paid by the due date, the person liable is obliged to pay interest on such amount for the period from the due date to the date the tax is paid.
2) The interest rate under Sub-Article (a) of this Article is set at 15% (twenty five percent) over and above the highest commercial banks, lending interest rate that prevailed during the preceding quarter.

## SECTION SEVEN

## Criminal Offences

**25.Procedure in Tax Offence Cases**

A tax offence under this Section is a violation of **the** criminal law of Ethiopia and shall be charged, prosecuted, and appealed in accordance with the Ethiopian Criminal Procedure Code.

**26.Tax Evasion**

A person who evades the declaration or payment of tax, commits an offence and, in addition to any penalty under Section 6, may be prosecuted and, on conviction, be subject to imprisonment for a term of not less than 5 (five) years.

**27.Making False or Misleading Statements**

1) A taxpayer who,

a/ Provided false or misleading information to a tax

ወይም አሳሳች መረጃ ያቀረበ ፣ወይም

ለ/ ለቢሮ ሠራተኛ ሊቀርብ ከሚገባው መግለጫ ውስጥ መግለጫውን አሳሳች ሊያደርግ በሚችል አኳኋን መካተት የሚገባቸውን ነጥቦች ያስቀረ እንደሆነ፣ የወንጀል ክስ ይመሠረትበታል።

2) የሐሰት መግለጫው የተሰጠው ወይም መካተት የሚገባው ነጥብ የተተወው ያለበቂ ምክንያት የሆነ እንደሆነ፣

ሀ/ የመግለጫው ትክክለኛ ያለመሆን ሊደርስበት ባለመቻሉ ሊከፈል የሚገባው ታክስ ከብር 1000(አንድ ሺ.ህ) በማይበልጥ አንሶ እንዲከፈል የሚያደርግ ከሆነ ታክስ ከፋዩ ከብር 10000 (አስር ሺ.ህ) ብር በማያንስ እና ከብር 20000(ሃያ ሺ.ህ) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከአንድ ዓመት በማያንስ እና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል።

ለ/ አንሶ እንዲከፈል የተደረገው ታክስ ከብር 1000 ሺ.ህ የሚበልጥ ከሆነ ከብር 20000 (ሃያ ሺ.ህ) በማያንስ እና ከብር 100,000(መቶ ሺ.ህ) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከሦስት ዓመት በማያንስ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡

3) የሐሰት መግለጫ የተሰጠው ወይም መካተት የሚገባው ነጥብ እንዲካተት ያልተደረገው ሆነ ተብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ፡-

ሀ/ የመግለጫው ትክክለኛ ያለመሆን ሊደረስበት ያለመቻሉ ሊከፈል የሚገባው ታክስ ከብር 1000 ሺ. በማይበልጥ አንሶ እንዲከፈል የሚያደርግ ከሆነ ታክስ ከፋዩ ከብር 50 ሺ.ህ በማያንስ እና ከብር 100,000 ሺ.ህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከአምስት

officer of the Bureau regarding a point in a material or in a particular statement,or

b/ omits points that should be included in the statement to be submitted to the a tax officer of the Bureau in a manner that any matter or thing without which the statement is misleading in a material, he will be charged with a crime.

2) Whether the false statement was made or the point that should have been included was omitted without sufficient reason;

a/ and if the inaccuracy of the statement un detected would have resulted in an underpayment of tax by an amount not exceeding 1,000 (one thousand) Birr, the taxpayer shall be subject to a fine of not less than 10,000 Birr and not more than 20,000 Birr and imprisonment for a term of not less than one (1) year and not more than three(3) years: and

b/ if the underpayment of the tax is in an amount exceeding 1,000 Birr, to a fine of not less than 20,000 birr and not more than 100,000 Birr, and to imprisonment for a term of not less than three (3) years and not more than five (5) years.

3) Where the false statement or omission is made knowingly or recklessly፡

a/ and if the inaccuracy of the statement were undetected would have resulted in an underpayment of tax by an amount not exceeding 1,000 Birr, the taxpayer shall be subject to a fine of not less than 50,000 Birr and not more than 100,000 Birr and to imprisonment for a term of not less than 5 (five) years and not more than 10 (ten) years; and

ዓመት በማያንስ እና ከአሥር ዓመት በማይበልጥ እሥራት የቀጣል፡፡

ለ/ አንሶ እንዲከፈል የሚደረገው ታክስ ከብር 1000 ሺ. የሚበልጥ ከሆነ ከብር 75,000 በማያንስ እና ከብር 200,000 ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከ10 ዓመት በማያንስ እና ከ15 ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

b/ if the underpayment of the tax is in an amount exceeding 1,000(one thousand) Birr, the tax payer shall be subject to a fine of not less than 75,000(seventy five thousand) Birr and not more than 200,000(two hundred thousand) Birr, and to imprisonment for a term of not less than 10 (ten) years and not more than 15 (fifteen) years.

**28. የቢሮን ሥራ ስለማሰናከል**

1) ማንኛውም ሰው፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ መሰረት ሥራውን በማከናወን ላይ ያለን የቢሮው ሠራተኛ ተግባር ያሰናከለ ወይም ለማስናከል የሞከረ፣ ወይም

ለ/ የአዋጁን አፈፃፀም በማናቸውም ሌላ አኳኋን ያሰናከለ ወይም ለማሰናከል የሞከረ እንደሆነ፣ ወንጀል መፈፀሙ ተረጋግጦ ሲፈረድበት ከብር 1000 ሺ. በማያንስ እና ከብር 100,000 ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና በሁለት ዓመት እሥራት ይቀጣል፡፡

2) ለንዑስ አንቀጽ/1/ አፈፃፀም የሚከተሉት እና እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች ተግባሮች የቢሮ ሥራ የማሰናከል ተግባራት ሆነው ይወሰዳሉ፣

ሀ/ የታክስ ከፋዩን ገቢ አስገኚ የሥራ እንቅስቃሴዎች የሚመለከቱ ሰነዶችን፣ ሪፖርቶችን ወይም ሌሎች ማናቸውንም መረጃዎች ለመመርመር ቢሮው ሲጠይቅ ፈቃደኛ ሆኖ ያለመገኘት፣

ለ/ ቢሮው ለጥያቄ እንዲቀርብ ሲያዝ ፈቃደኛ ሆኖ ያለመገኘት፣

ሐ/ የቢሮው ሠራተኛ ወደ ታክስ ከፋዩ የንግድ ሥራ

**28.Obstruction of Tax Administration**

1) Any person who:

a/ obstructs or attempts to obstruct an officer of the Bureau in the performance of duties under this Proclamation, or

b/ otherwise impedes or attempts to impede the implementation of the Proclamation,commits an offence and is liable, on convic- tion, to a fine of not less than 1,000 Birr and not more than 100,000 Birr, and to imprisonment for a term of two (2) years,

2) For the purposes of sub-article /1/of this Article, the following and other similar acts shall be considered acts of obstruction of office work::

a/ refusal to satisfy the request of the Bureau for inspection of documents, repmts, or other information relating to a taxpayer's income producing activities;

b/non compliance with the Bureau's request to report for an interview;

c/ interference with a tax officer's right to enter the taxpayer's business

| | |
|---|---|
| ቦታ ለመግባት ያለውን መብት መገደብ፡፡ | premises. |
| **29. ለውጥን ያለማስታወቅ** | **29.Failure to Notify** |
| በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 በሚያዘው መሰረት በሁኔታዎች ላይ የተደረጉ ለውጦች ለቢሮ ያላስታወቀ ማናቸውም ሰው ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ፡- | Any person who fails to notify the Bureau of changes in circumstances as provided for in Article 17 of this Proclamation shall, upon conviction by a court of law: |
| ሀ/ ጥፋቱ የተፈፀመው ሆን ተብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ ከብር 10,000 ሺ. በማያንስ የገንዘብ መቀጫ እና በአንድ ዓመት እሥራት፣ | a/where the failure was made knowingly or recklessly, is liable to a fine of not less than 10,000(ten thousand) Birr and to imprisonment for one year;or |
| ለ/ በሌሎች ሁኔታዎች ከብር 5 ሺ. በማያንስ የገንዘብ መቀጫ እና በአንድ ወር እሥራት ይቀጣል፡፡ | b/ in any other cases, to a fine of not less than 5,000(five thousand) Birr and to imprisonment for a term of six months. |
| **30.በቢሮ ሠራተኛ የሚፈፀሙ ጥፋቶች** | **30.Offences by Tax Officer** |
| 1) የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም በቢሮው የተቀጠረ ሠራተኛ ወይም የቀድሞ ተቀጣሪ የነበረ፣ | 1) Any tax officer or former taxation officer employed in carrying out the provisions of this Proclamation, who: |
| ሀ/ በህግ መሰረት ሊያገኘው ከሚገባ ክፍያ ወይም ሽልማት ውጪ ከተቀጠረበት ተግባር ጋር በተያያዘ ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የገንዘብ ወይም ሌላ ዓይነት ክፍያ ወይም ስጦታ እንዲደረገለት የጠየቀ ወይም የተቀበለ፣ ለክፍያው ወይም ለስጦታው ተስፋ ወይም መያዣ የጠየቀ ወይም የተቀበለ፣ ወይም | a/ directly or indirectly asks for, or receives in connection with any of the taxation officer's duties, a payment or reward, whether pecuniary or otherwise, or promise or security for that payment or reward, not being a payment or reward which the officer is law- fully entitled to receive, or |
| ለ/ ከታክስ በሚገኘው ገቢ ላይ ማጭበርበር ወይም ከዘህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር ወይም ከተሰጠው ኃላፊነት መልካምአፈፃፀም፣ማድረግ የሚገባውን ከማድረግ ለመታቀብ፣ ተገቢ ያልሆነን ነገር ለመፍቀድ፣በታክስ ላይ የሚፈፀመን የማጭበርበር ተግባር ለመደበቅ፣ ወይም በሚስጥር ለመተግበር | b/enters into or acquiesces in an agreement *to* do or to abstain from doing, permit, conceal, or connive at any act or things where by the tax revenue is or may be defrauded or which is contrary to the provisions of this Proclamation or to the proper execution of the taxation officer's duty commits an offence and is liable |

ውል የገባ ወይም በሚገባ ማናቸውም ውል ውስጥ በዚህ ተግባር መተባበሩን የሚያሳይ ስምምነት የሰጠ፣ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 50 ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከ10 ዓመት በማያንስ ከ20 ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

2) የቢሮው ሠራተኛ የሆነ ወይም የነበረ እና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም የተቀጠረ፣ በኢትዮጵያ ንግድ ህግ በንግድ ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ ከታዘዘው ዓይነት መረጃ በስተቀር፣

ሀ/ታክስን በማስፈፀም ረገድ ባለው ሥልጣን ወይም ግዴታ መረጃ ለማናቸውም ሌላ ሰው ወይም የዚያ ሰው ወኪል ለሆነ ሰው አሳልፎ የሰጠ፣

ለ/ በዚህ አዋጅ መሰረት ታክስን በማስፈጸም ረገድ ያለውን ሥልጣን ለመጠቀም ወይም የሥራ ግዴታውን ለመወጣት እንዲያስችል በቢሮው ዘንድ የሚገኘውን ማናቸውንም መረጃ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካልሆነ በስተቀር ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፣ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 10,000 ሺ በማያንስ የገንዘብ መቀጫ እና ከሁለት ዓመት በማያንስ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡

3) የቢሮ ሠራተኛ ያለበቂ ምክንያት ጉዳዩን በማንተት በግብር ከፋይ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት

on conviction to a fine of not more than 50,000(fifty thousand) Birr and to imprisonment for a term of not less than 10 (ten) years and not more than 20 (twenty) years.

**2)** A tax officer or a former tax officer engaged in carrying out the provisions of this Proclamation, except such information is required by the Commercial Code of Ethiopia to be published in the Trade Gazette, who,

a/discloses to any person or his representative, any matter in respect of another person, that may, in the exercise of the taxation officer's powers or the performance of the taxation officer's duties under the said provisions, come to the taxation officer's knowledge; or

b/ permits any other person to have access to records in the possession or custody of the Bureau, except in the exercise of the taxation officer's powers or the performance of the other's duties under this Proclamation or by order of a court; commits an offence and is liable on conviction to a fine of not less than 10,000 Birr and to imprisonment for a tenn of not less than two (2) years and not **more** than five (5) years.

3) The Bureau officer shall be held responsible for any damage coused to a

በፍትሐብሔር ያለበት ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል፡፡

4) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ የቢሮው ሠራተኛ :-

ሀ/ ማናቸውንም ሰነድ ወይም መረጃ፡-

/i/ ለዚህ አዋጅ ወይም ለማናቸውም ገንዘብ ነክ አዋጅ አፈፃፀም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ፣

/ii/ በህግ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት አስፈላጊ ሲሆን፣ ለዋናው ኦዲተር፣

/iii/ መረጃ ለመለዋወጥ፣ ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት ኢትዮጵያ ከሌሎች አገሮች ጋር ባደረገችው ስምምነት መሰረት አግባብ ላላቸው የሌሎች አገሮች ባለሥልጣኖች፣

/iv/ በህግ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት አስፈላጊ ሲሆን ለሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን፣

/v/ ከዚህ በላይ ላልተገለፀ ለማናቸውም ህግ አስፈጻሚ መ/ቤት ግዴታውን ለመፈፀም የሚያስችለው መረጃ እንዲሰጠው ከቢሮው በጽሁፍ ሲታዘዝ ፡፡

ለ) ኃላፊነታቸውን ለመወጣት አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ አንድን ሰው ለይተው የማይጠቅስ መረጃዎች ለማናቸውም በመንግስት ገቢ ስራ ላይ ለሚያገለግል እና ለስታትስቲክስ መ/ቤት ሠራተኛ ከመስጠት አያግደውም፡፡

**31.ሳይፈቀድ ታክስ ስለመሰብሰብ**

ማናቸውም ሰው በዚህ አዋጅ መሰረት ሳይፈቀድለት ታክስ ወይም እንደታክስ የሚታይ ሌላ ክፍያ የመሰበሰብ ወንጀል የፈጸመ ወይም ለመሰብሰብ የሞከረ ጥፋተኝነቱ በፍርድ ቤት

tax payer by delaing ,without any good couse, the performance of his duty such employee inaddition to being held liable for the damages and shall be held according to the law of the land.

4) Nothing in this Article shall prevent a taxation officer from disclosing:

a/any document or information to:

/i/any person where the disclosure is necessary for the purposes of this Proclamation or any other fiscal low;

/ii/ the Auditor-General where the disclosure is necessary for the performance of duties entrusted to it by law; •

/iii/ the competent Bureau of the government of another country with which Ethiopia has entered into an agreement for the avoidance of double taxation or for the exchange of information, to the extent permitted under the agreement;

/iv/ the Ethics and Anti-Corruption Commission where the disclosure is necessary for the performance of duties entrusted to it by law;

/v/ a law enforcement agency not described above, where the Minister of Revenue issues written authorization to. make dis- closures necessary for the enforcement of the laws under the agency's Bureau;

b/ any person in the service of the State in a revenue or statistical department, information which does not identify a specific person where such disclosure is necessary for the performance of the person's official duties.

**31. Unauthorized Tax Collection**

Any person not authorized to collect tax under this Proclamation who collects or attempts to collect tax (or an amount the person describes as tax) commits an

| | |
|---|---|
| ሲረጋገጥ ከብር 50 ሺ የማያንስ የገንዘብ መቀጫ እና ከአምስት ዓመት በማያንስ ከአስር ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፡፡ | offence and is liable. on conviction to a fine of not less $an 50,000 Birr and to imprisonment for a term of not less than five (5) years and not more than ten (l0) years. |
| **32. መርዳት ወይም ማበረታታት** | ***32.*Aiding or Abetting** |
| ማናቸውም ሰው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንዲጣስ የረዳ፣ ያበረታታ፣ያነሳሳ፣ ወይም በሚስጥር የተባበረ እንደሆነ እንደዋንኛው ጥፋተኛ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመጣስ ጥፋት ይፈጽማል፡፡ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የፈጸመ ሰው፣ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ እርዳታውን ወይም ትብብሩን ለሰጠበት ጥፋት ከተወሰነው የገንዘብ እና የእሥራት ቅጣት ባልበለጠ በገንዘብ እና በእሥራት ይቀጣል፡፡ | A person, who aids, abets, incites, or conspires with another person, to commit a violation of this Proclamation, also commits an offence. He may be subject to prosecution a.nd, on conviction, be liable to a fine and imprisonment, not in excess of the amount of fine or period of imprisonment provided for the offence aided or abetted. |
| **33.በድርጅቶች የሚፈጸም ጥፋት** | **33.Offences by Entities** |
| 1) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አንድ ድርጅት ይህንን አዋጅ በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ እንደሆነ ጥፋቱ በተፈጸመ ጊዜ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የሆነ ማናቸውም ሰው በድርጅቱ የተፈጸመውን ጥፋቱ እንደፈጸመ ተቆጥሮ በዚህ አዋጅ የተጣለው ቅጣት ተፈጻሚ ይሆንበታል፡፡ | 1) Subject to Sub-Article (3) of this Article, where. an entity commits• an offence, the person who is a manager of that entity at the time the offence is committed, is treated as also having committed the same offence and is liable to a fine and imprison- ment under this Proclamation. |
| 2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ማናቸውም ድርጅት በዚህ አዋጅ መሰረት ሊከፍል የሚገባውን ታክስ ወይም አዋጁ እንደታክስ የሚቆጥረውን ማናቸውም ሌላ ክፍያ ገቢ ሳያደርግ የቀረ እንደሆነ ጥፋቱ በተፈፀመበት ጊዜ ወይም ከተፈጸመበት ጊዜ አስቀድሞ በነበሩት ስድስት ወራት ውስጥ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የነበሩ ሰዎች ከድርጅቱ እና ከሌላ ሰው ጋር በአንድነትና በተናጠል ቢሮው ለሚፈልገው ታክስ እና ሌሎች ክፍያዎች ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡ | 2) Subject t to Sub-Article (3) of this Article, where an entity commits an offence by failing to pay an amount of tax, including an amount treated by this Proclamation as though it were tax, the person who was a manager of that entity at the time of such failure or was a manager within six (6) months prior to the date of commission is jointly and severally liable with that entity and that other person for the amount due to the Bureau. |

3) በንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ የተደነገጉት፣

ሀ/ ጥፋቱ የተፈጸመው ግለሰቡ ሳያውቅ ወይም ሳይስማማበት ከሆነ፣

ለ/ አንድ ነገሮችን በጥንቃቄ የሚያይ ሰው በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የጥፋቱን መፈጸም ለመከላከል ይወስዳቸዋል ተብሎ የሚገመቱ ጥንቃቄዎችን፣ ተገቢውን ትጋት እና የአሠራር ጥበብ የተሞላበት እርምጃ ግለሰቡ ወስዶ የተገኘ እንደሆነ፣ ተፈጻሚ አይሆኑበትም፡፡

4) ለንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ አፈፃፀም "ሥራ አስኪያጅ" ማለት

ሀ/ የሽርክና ማህበርን በሚመለከት የሽርክናው ማህበር አባል ወይም የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ወይም ከሁለት ኃላፊነቶች በአንዱ እንደሚሠራ ሆኖ የሚታይ፣

ለ/ ኩባንያን በሚመለከት የኩባንያው ሥራ መሪ፣ ሥራ አሥኪያጅ ወይም ማናቸውም ሌላ ሹም ወይም ከእነዚህ ኃላፊነቶች በአንዱ እንደሚሠራ ሆኖ የሚታይ፣

ሐ/ የሰዎችን ህብረት በሚመለከት የህብረቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም ማናቸውም ሌላ ሹም ወይም ከእነዚህ ኃላፊነቶች በአንድ እንደሚሠራ ሆኖ የሚታይ ነው፡፡

## 34.በተረካቢዎች የሚፈጸም ጥፋት

1) ማናቸውም ሰው በአንቀጽ 16 ንኡስ አንቀጽ /4/ በተደነገገው መሰረት ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ፣ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ብር 5,000/አምስት ሺህ ብር/ የገንዘብ መቀጫ እና በአንድ ዓመት እሥራት ይቀጣል፡፡

2) ማናቸውም ሰው አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ /4/ መሰረት ለታክስ ክፍያ የሚውለውን ገንዘብ ለይቶ ባለማስቀመጡ ምክንያት በንዑስ አንቀጽ /1/ መሰረት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፣ፍርድ ቤቱ ከገንዘብና እሥራት መቀጫው በተጨማሪ ለይቶ ያላስቀመጠውን የገንዘብ መጠን ለታክስ ቢሮ ገቢ እንዲያደርግ ሊያዝ ይችላል፡፡

3) Sub-Articles (l)and(2) do not apply where,

a/ the offence is committed without that person's knowledge or consent; and

b/ that person has exercised the degree of care, diligence and skill that a reasonable prudent person would have exercised in comparable circumstances to prevent the commission of the offence.

4) In Sub-Articles (1) and (2), "manager" shall mean;

a/in the case of a partnership a partner or manager of the partnership or a person purpor- ting to act in either of those capacities;

b/ in the case of a company, a director, manager, or officer of the company or a person purporting to act in any of those capacities;

c/ in the case of an association of persons, a manager or a person purporting to act in that capacity.

## 34.Offences by Receivers

1) A person who fails to comply with the requirements of Article 16(4) commits an offence and is liable, on conviction to a fine of 5,000 Birr and to imprison- ment for a term of one (1) year.

2) Where a person is convicted of an offence under Sub Article (1) of this Article for failing to set aside an amount as required under Article 16(4), the court may, in addition to imposing a fine and prison sentence, order. The convicted person to pay, to the Bureau , an amount not exceeding thr amount which the person failed to set aside. shall specify:

## 35.የጥፋተኞችን ስም በጋዜጣ አትሞ ስለማውጣት

1) ቢሮው በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 25 እስከ አንቀጽ 34 የተደነገጉትን የወንጀል ጥፋቶች በመፈጸም የተፈረደባቸው ሰዎች ስም ዝርዝር በየጊዜው በዕለታዊ ጋዜጦች ታትሞ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሰረት ታትሞ የሚወጣው ዝርዝር፣

ሀ/ የድርጅቱን ወይም የግለሰቡን ስም እና አድራሻ፣

ለ/ ቢሮው ተገቢ ነው ብሎ የሚያምንበትን የወንጀል አፈጻጸም ዝርዝር፣

ሐ/ ጥፋቱ የተፈጸመበትን የግብር ዘመን ወይም ዘመኖች፣

መ/ ሳይከፈል የቀረውን የግብር መጠን፣

ሠ/ በተጨማሪ እንዲከፈል የተወሰነበት ግብር ካለ ይህንኑ፣

## ክፍል ስምንት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 36.በኤሌክትሮኒክስ ዘዴዎች ስለመጠቀም

ቢሮው በዚህ አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት በሚወጣው ደንብ የተዘረጋውን የተርን ኦቨር ታክስ አስተዳደር ሥርዓት ይበልጥ ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ የኤሌክትሮኒክ ዘዴዎች በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፡፡

## 37.የመተባበር ግዴታ

1) ይህንን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል እንዲቻል አግባብ ያለው የፌዴራል እና የክልል መንግሥታት ባለሥልጣኖችና ወኪሎቻቸው በተጨማሪም ድረጅቶች፣የቀበሌ መስተዳድሮች እና ማህበራት ሁሉ

## *35.* publishing the names of Convicted

1) The Bureau shall from time to time publish by notice in a Gazette a list of persons who have been convicted of offences under any of the provisions of Articles *25* to 34 of this proclamation.

2) The list published in terms of Sub-Article (1)

a/ the name, address, and principal enterprise of the person;
b/ such particulars of the offence as the Bureau may think fit;
c/ the tax period or tax periods· in which the offence occurred;
d/ the ·amount or estimated amount of the tax evaded; and
e/ the amount, if any, or the additional tax imposed.

## SECTION EIGHT
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 36.Using Electronic Transaction

The Bureau will promote the widespread use of electronics method to make the turnover tax management system more efficient and effective under this proclamation and regulations issued pursuant to the decree.

### 37. Duty to Cooperate

1) All Federal and Regional government authorities and their agencies, Bodies, Kebcle Administrations and Associations shall have the duty to cooperate with the Bureau in the enforcement of this Proclamation.

ከታክስ ቢሮ ጋር በመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

2) የዚህ አንቀፅ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፤-

ሀ/ በይግባኝ ቀጠሮ ላይ ካልሆነ ወይም ቢሮው የተራዘመ የታክስ መክፈያ ጊዜ ካልሰጠ በስተቀር፣ ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ግብር በወቅቱ የከፈለ ስለመሆኑ ወይም አዲስ ታክስ ከፋይን በሚመለከት የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ካላቀረበ በስተቀር፣ፈቃድ ሰጪ አካል፣ማዘጋጃ ቤት አዲስ የንግድ ሥራ ፈቃድ መስጠት ወይም ማደስ አይችልም፡፡

ለ/ ቢሮው ታክስ ከፋዩ ያለበትን ግዴታ ስለመፈጸሙ የምስክር ወረቀት የማይሰጥ ሲሆን ስለዚሁ ያለውን ምክንያት በመዘርዘር ለጠያቂው ይሰጣል፡፡

ሐ/ የምስክር ወረቀት አልሰጥም በማለቱ ወይም የንግድ ሥራ ፍቃድ በመሰረዙ የግብር አስገቢው ቢሮ በሰጣቸው ምክንያቶች ቅር የተሰኘ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ቅሬታውን ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## 38.የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ስልጣን

በዚህ አዋጅ በሌሎች አንቀፆች ከተገለፀው በተጨማሪ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ለኢኮኖሚ፣ ለማህበራዊ ወይም ለአስተዳደራዊ ምክንያቶች ወይም በክልሉ ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 19 /2016 አንቀጽ 63 ንዑስ አንቀጽ 2 በተዘረዘሩት ምክንያቶች በዚህ አዋጅ ከተጣለው ታክስ ክፍያ በሙሉ ወይም በከፍል ነፃ የማድረግ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## 39. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1) አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው መስተዳደር ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

2) ቢሮው ለዘህ አዋጅ አፈጻጸም የሚረዱ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 40.ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

ይህን አዋጅ የሚቃረን ሌላ ማንኛውም ድንጋጌ በዚህ አዋጅ

2) Without prejudice to the general provisions of this Article;-

a/ No Ministry, Municipality, Department or Office of pie Federal *or* Regional Government shall issue or renew any license to any tax payer unless the applicant produces a certificate from the Bureau to the effect, that tax due in respect of the preceding year or years have been paid, or where the taxpayer is seeking license for the first time a taxpayer-identification number (TIN) issued by the Bureau unless an appeal .is pending, or time for payment is extended by the Bureau.

b/ If the Bureau 'refuses to issue a certificate it shall, on demand by the applicant for the license, provide him or it with a written statement of its reasons therefore.

c/ Any taxpayer who is dissatisfied with the reasons given by the Bureau for refusing to issue a certificate or canceling a business license may submit his complaint to the Complaints Investigation Department.

## 38.Power of the Regional state

In addition to what is stated in other Articles of this proclamation, the Regional Executive Council is empowered to exempt all or part of the tax imposed by this proclamation for economic, social or administrative reasons or for the reasons listed in Article 63, Sub-Article 2 of the Regional Income Tax Proclamation No. 19/2023.

## 39.Power to Issue Regulations and Directives

1) The Executive Council may, when it deems necessary, issue Regulations for the implementation of this Proclamation.

2) The Bureau may issue Directives for the implementation of this Proclamation.

## 40. Inapplicable Laws

Any other provision that contradicts this Proclamation shall

በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

**41.የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

ይህ አዋጅ ከመጽደቁ በፊት በነበሩ ሕጎች መሠረት ሳይከፈል የቀረ የተርን ኦቨር ታክስ ዕዳዎች በዚህ አዋጅ መሰረት የሚሰበሰብ ይሆናል፡፡

**42.አዋጅ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት ከፀደቀበት ከታህሳስ 5 ቀን 2016.ዓ.ም ጀምሮ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አርባ ምንጭ**

**ታህሳስ 5 ቀን 2016 ዓ.ም**

**ጥላሁን ከበደ**

**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳደር**

not apply to the matters covered by this Proclamation.

**41.Transitory Provisions**

Turnover tax debts that remained unpaid under the laws in force prior to the enactment of this Proclamation shall be collected pursuant to this Proclamation.

**42. Effective Date**

This proclamation shall come into force on, December 14, 2023, upon its approval by the South Ethiopia Regional State Council.

**Done at Arba minch, on December14, 2023.**

**Tilahun Kebede**

**President of South Ethiopia**

**Regional State**

8

1

2

9

1

1

1